የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ዲንካራ ጋዜጣ

AFAR REGION DINKARA GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

6ኛ ዓመትቁጥር 44

ሠመራ ሰኔ 2000 ዓ.ም

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ምክር ቤት ጠባቂነት

6th Year No. 44

Semera

ማውጫ

የከተማና የገጠር ንፁህ የመጠጥ ውሀና ፍሳሽ አገልግሎት እንደገና

ለማደራጀት የወጣ አዋጅ..... ገጽ 1

አዋጅ ቁጥር 44/2 ዐዐዐ ዓ.ም

የከተማና የገጠር ንፁህ የመጠጥ ውሀና ፍሳሽ አገልግሎት እንደገና ለማደራጀት የወጣ አዋጅ

መግቢያ

በክልሉ ያለውን ያልተማከለ የወረዳና የከተማ አስተዳደር ስርአትን መሰረት በማድረግ በከተማና በገጠር የንፁህ ውሀና ፍሳሽ አገልግሎት የተሻለ የአሰራር ስርአት እንዲኖር በማስፈለጉ፣

አሁን በስራ ላይያለው አዋጅ አሁን ካለው የመንግስት አደረጃጀት ጋር አብሮ የማይሄድ በመሆኑና በከተሞችና በገጠር አካባቢዎች ያለው የንፁህ መጠጥ ውሀ አገልግሎት በአዲስ መልክ በማደራጀት ተቋማቱ በራሳቸው ገቢ እንዲተዳደሩ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ መሰረት የሚከተለው ታውጇዋል።

ጠቅላላ

አንቀጽ 1

አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የከተማና የገጠር የንፁህ መጠጥ ውሀና ፍሳሽ አገልግሎት እንደገና ለማደራጀት የወጣ አዋጅ ቁጥር 44/2 ዐዐዐ ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

አንቀጽ 2

ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ ፡-

1. ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ማለት በአዋጅ ቁጥር 3 ዐ/98 አንቀጽ 7 መሰረት የተቋቋመው የክልሉ አስፈጻሚ አካላት /ካቢኔ/ም/ቤት ነው።
2. ወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት ማለት በአዋጅ ቁጥር 35/98/አንቀጽ 3 መሰረት የተቋቋመው የወረዳ አስፈጻሚ አካላት ም/ቤት ነው ።
3. የውሀ አገልግሎት ማለት የከተማና የገጠር ቀበሌዎች የንፁህ መጠጥ ውሀና ፍሳሽ አገልግሎት ማለት ነው።
4. '' የከተማ አስተዳደር'' ማለት በአዋጅ ቁጥር 33/98 የተቋቋመውን የሠመራ ከተማ አስተዳደርና በአዋጅ ቁጥር 34/98 አንቀጽ 5/3/ መሰረት የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ወደ ፊት የሚቋቋመው የከተማ አስተዳደር ነው።
5. '' ቦርድ'' ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 መሰረት የውሀ አገልግሎት ጽ/ቤትን በበላይነት የሚመራ አካል ነው።
6. '' ከተማ'' ማለት በአዋጅ ቁጥር 34/98 አንቀጽ 2/1/ መሰረት ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመባቸው ወይም በክልል መንግስት መመዘኛ ከተማ የሚል ስያሜ ያገኘ ማናቸውም አካባቢ ነው።
7. '' ቀበሌ'' ማለት በክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 88 መሰረት የተቋቋመ የመጨረሻ የአስተዳደር እርከን ነው።
8. '' ማዘጋጃ ቤት'' ማለት በአዋጅ ቁጥር 34/98 አንቀጽ 2/2 መሰረት ትርጓሜ የተሰጠውና ተጠሪነቱ ለታቀፈበት ወረዳ የሆነ በራሱ ገቢ የሚተዳደር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ሰጭ ተቋም ነው።
9. ''ጽ/ቤት'' ማለት በዚህ አወጅ አንቀጽ 9 መሰረት የተቋቋመና ለከተማው ህብረተሰብ የመጠጥ ውሀና ፍሳሽ አገልግሎት የሚሰጥ የውሀ አገልግሎት ጽ/ቤት ነው።
10. '' ቢሮ'' ማለት የክልል የውሀ ሃብት ልማት ቢሮ ነው።

አንቀጽ 3

<u>የውሃ አገልግሎት አስተዳደርን ስለማቋቋም</u>

1. በዚህ አዋጅ በክልሉ በሚገኙት አምስት ዞኖች ውስጥ ባሉ ከተሞች ከዚህ እንደሚከተለው የውሃ አገልግሎት አስተዳደር ተቋቁሟል።

   ሀ/ አወሲ ረሱ ---------- አይሣኢታ፣ዱብቲ፣ሚሌ

   ለ/ ኪልበቲ ረሱ ---------- አብአላ

   ሐ/ ገቢ ረሱ -------- አዋሽ 7 ኪሎ፣ መልካ ወረር፣መልካ ሰዲ/ሲዲሀ ፋጌ/ ገዋኔ፣አዋሽ አርባ

   መ/ ፈንቲ ረሱ ---------- ከልዋን

   ሠ/ ኘሪ ረሱ ---------- ዳሊፋጌ

2. በዚህ አዋጅ የሠመራ ሎጊያ ውሃ አገልግሎት አስተዳደር ተቋቁሟል።
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የወረዳ መስተዳድር ም/ቤቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር በወረዳው በሚገኙ ከተሞችና ገጠር ቀበሌዎች የውሃ አገልግሎት አስተዳደር ሊያቋቁሙ ይችላሉ።

<u>አንቀጽ 4</u>

<u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ በሚገኙ የከተማና የገጠር ቀበሌዎች ውሃ አገልግሎት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>የውሃ አገልግሎት አስተዳደር ስለማደራጀት፣ ቦርድና ጽህፈት ቤት</u>

<u>ስለማቋቋም</u>

<u>አንቀጽ 5</u>

<u>የውሃ አገልግሎት አስተዳደርን ስለማደራጀት</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ስር በተገለፁት በእያንዳንዱ ከተማ ከዚህ የሚከተሉት የውሃ አገልግሎት አስተዳደር አካላት ይኖራሉ።

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 እና 8 መሰረት የሚቋቁም የውሀ አገልግሎት ቦርድ
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 መሰረት የሚቋቋም የውሀ አገልግሎት ጽ/ቤት
3. ሌሎች አስፈላጊ የስራ ክፍሎች

አንቀጽ 6

የውሀ አገልግሎት አስተዳደር ቦርድን ስለማቋቋም

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ስር የተገለጸው ከተማ ከዚህ በሚከተለው መልኩ የውሀ አገልግሎት አስተዳደር ቦርድ አባላት ይኖረዋል።

   ሀ/ ከተማው የታቀፈበት ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ ---------- ሰብሣቢ

   ለ/ የወረዳው የውሀ ሃብት ጽ/ቤት ኃላፊ ---------- ም/ሰብሣቢ

   ሐ/ የወረዳው የፋይናንስና ኢ/ጽ/ቤት ኃላፊ ---------- አባል

   መ/ የከተማው ማዘጋጃ ቤት ሹም/ስራ አስኪያጅ/---------- አባል

   ሠ/ ከከተማው የንግድ ማህበረሰቡ ሁለት ተወካዮች ------ አባል

   ረ/ ከከተማው ነዋሪ የሚወከሉ ሁለት የውሃ አገ/ተጠቃሚ ተወካዮች ---- አባል

   ሸ/ ከከተማው የከፍተኛ ጤና ተቁም ጎላፊ /ተወካይ/ ---------- አባል

   ቀ/ የከተማው ውሀ አገልግሎት ጽ/ቤት ኃላፊ ---------- ፀሐፊ

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 /ቀ/ላይ የተገለጸው የከተማው ውሀ አገልግሎት ጽ/ቤት ኃላፊ በፀሐፊነት ያገለግላል በቦርድ ስብሰባዎች ላይ ያለ ድምጽ ይሣተፋል ሣብና አስተያየት ይሰጣል።
3. የከተማው የውሀ አገልግሎት ቦርድ ተጠሪነቱ ለታቀፈበት ወረዳ። መስ/ም/ቤት ይሆናል።
4. የቦርዱ አባላት የስራ ዘመን የወረዳው መስተዳድር የስሪ ዘመን ይሆናል። ሆኖም አባላቱ በጠቅላላ ወይም ከአባላቱ አንዳንዶቹ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ሳይወጡ ሲቀሩ መስተዳድር ም/ቤቱ አፈጻጸማቸውን በመገምገም ሊለውጣቸው ይችላል።
5. ቦርድ በየሁለት ወሩ መደበኛ ስብሰባውን ከከተማና ከንግዱ ማህበረሰብ የተወከሉትን አራት አባላት ጨምሮ ከአባላቱ 2/3 ኛው ከተገኙ ሊያካሄድ ይችላል።

አንቀጽ 7

የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

የቦርዱ ስልጣንና ተግባር ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል።

1. ጽ/ቤቱን ያደራጃል፣ በበላይነት ይመራል
2. የውሀ አገልግሎት ጽ/ቤት አዘጋጅቶ የሚያቀርብለትን አመታዊ የስራ ዕቅድና በጀት መርምሮ ያፀድቃል ተግባራዊ አፈጻጸሙንም ይከታተላል ይቆጣጠራል።
3. የጽ/ቤቱን አመታዊ የገንዘብ ነክና አጠቃላይ የስራ አፈጻጸም ሪፖርቶችን ይገመግማል በታዩ ችግሮች ላይ ተገቢና ህጋዊ ውሳኔዎችን ይወስናል ለሚመለከታቸው አካላትም ያሳውቃል።
4. የውሀ አግልግሎት ጽ/ቤት ኃላፊን ይመድባል የስራ አፈጻጸሙን ይገመግማል እምነት ሲያጣበትም ከኃላፊነት እንዲነሳ ከበቂ መግለጫ ጋር ለወረዳ መስተዳድር ም/ቤት ወይም ለከተማ መስተዳድር ም/ቤት ያቀርባል።
5. ለመጠጥ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጥንካሬና እድገት የሚያግዙ የተለያዩ የገንዘብና የቁሣቁስ ምንጮች ያፈላልጋል።
6. ልዩ ልዩ የአበልና ጥቅማ ጥቅም ጥያቄዎችን እየመረመረ ውሣኔ ይሰጣል
7. የመጠጥ ውሀ ታሪፍ በጽ/ቤቱ ተጠንቶ ሲቀርብለት መርምሮ ተጠሪ ለሆነለት አካል ለወሣኔ ያቀርባል ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል።
8. የንፁህ ውሀ ተጠቃሚውን ህብረተሰብ በማወያየት የተሻለና ቀልጣፋ አሰራር ተቀርጾ በጽ/ቤቱ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል።
9. ለአዳዲስ ግንባታ ስራዎች የሚያስፈልገውን በጀት በተመለከተ ተጠሪ ለሆነለት ወረዳ መስተዳድር ም/ቤት ወይም ለከተማው አስተዳደር ም/ቤት አቅርቦ ያፀድቃል አፈጻጸሙን ይከታተላል ይቆጣጠራል።
10. መደበኛና አስቸኳይ ስበሰባዎችን በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት ያካሂዳል።
11. ወቅታዊና መደበኛ ሪፖርቶችን ተጠሪ ለሆነለት አካል ያቀርባል።

አንቀጽ **8**

የቦርድ ሰብሳቢና ስልጣንና ተግባር

1. የቦርዱ ሰብሳቢ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ላይ የተደነገገውን የቦርዱን ስልጣንና ተግባር በበላይነት ይመራል ይከታተላል የቆጣጠራል
2. የቦርዱ ም/ሰብሳቢ ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ የቦርዱን ስልጣንና ተግባራት ያከናውናል ይመራል ይቆጣጠራል።
3. በሁኔታዎች አጋጣሚ ሰብሳቢውና ም/ሰብሳቢው በማይኖሩበት ጊዜ መደበኛ ወይም አስቸኳይ የሆነውን ስብሰባ ለመምራት በቦርዱ አባላት አብላጫ ድምጽ የተመረጠው አባል ይመራል።
4. ሰብሳቢውም ሆነ አመራሩ በውክልና በሚሰጥ ኃላፊነት ሊመራ አይችልም።

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ውሳኔ የሚያስፈልገው ጉዳይ የቦርዱን አብላጫ ድምጽ መሰረት አድርጐ መፈጸም አለበት። የተሰጠው ድምጽ በሁለት ወገን እኩል ድምጽ ሲያጋጥም ሰብሳቢው የደገፈው ወገን አሸናፊ ይሆናል፤፤

<u>አንቀጽ **9**</u>

<u>በከተማው አስተዳደር የውሃ አገልግሎት ቦርድ ስለማቋቋም</u>

1. በዚህ አዋጅ የሠመራ ከተማ አስተዳደር ወይም ወደፊት የከተማ አስተዳደር ደረጃ ሊሰጠው የሚችል ከተማ ከዚህ የሚከተለው አባላትን ያካተተ ቦርድ ይኖራል።

ሀ/ የከተማው ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ስሪ አስኪያጅ ---------- ሰብሳቢ

ለ/ የከተማው አስተዳደር የውሀና ፍሳሽ ጽ/ቤት ኃላፊ ---------- ም/ሰብሳቢ

ሐ/ የከተማው አስተዳደር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ጽ/ቤት ኃላፊ ------- አባል

መ/ የከተማው የንግድ ማህበረሰብ ሁለት ተወካዮች ---------- አባል

ሠ/ ከከተማው ነዋሪ ሁለት ተወካዮች - ---------- አባል

ረ/ ከከተማው የከፍተኛ ጤና ጣቢያ /ማእከል/ ኃላፊ ---------- አባል

ሸ/ የውሀ አገልግሎት ጽ/ቤት ኃላፊ --- ፀሐፊ

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ፣7 ፣እና 8 ስር የተገለፁትን ንዑስ አንቀጾች በከተማ እየሰጣቸው በአግባቡ ይገለገልበታል።
3. በከተማው አስተዳደር የሚቋቋመው የውሀ አገልግሎት ቦርድ ተጠሪነቱ ለከተማው አስተዳደር ም/ቤት ይሆናል።

<u>አንቀጽ **10**</u>

<u>የውሃ አገልግሎት ጽ/ቤት ስለማቋቋም</u>

1. የውሃ አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ስር በተዘረዘሩት ከተሞች የሚቋቋም ሆኖ አንድ ጎላፊና ሌሎች ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች እንዲኖሩት ተደርጐ ይደራጃል።

2. የጽ/ቤቱ ተጠሪነት ለቦርዱ ይሆናል ሞያዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ለወረዳው የውሃ ሃብት ጽ/ቤት ተጠሪ ይሆናል።

አንቀጽ 11

የጽ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

1. አገልግሎቱ ለተቋቋመበት ከተማ ነዋሪ ንጽህናውንና ጥራቱን የጠበቀ ውሃ በበቂ መጠን ያቀርባል።
2. የመጠጥ ውሃ አገልግሎት ለሚጠይቁ ተጠቃሚ ግለሰቦችና ድርጅቶች እንደ ጥያቄው ቅደም ተከተል የውሃ መስመሮችን ያስገባል ቢበላሹም ይጠግናል።
3. በስራ ላይ ባለው ታሪፍ መሠረት ከመጠጥ ውሃና ፍሳሽ እንዲሁም ከሌሎች የተለያዩ አገልግሎቶች የሚገኙትን ገቢዎች በመገባ ይሰበስባል።
4. በቦርዱ የቅድሚያ እውቅናና ፈቃድ ማናቸውም እርዳታና ስጦታ በአገልግሎቱ ስም ይቀበላል።
5. ከቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን ማሽነሪዎች ተሽከርካሪዎችና መሰል መገልገያ መሳሪያዎች ይገዛል።
6. ለመጠጥ ውሃና ስርጭት አገልግሎት የተተከሉ የውሃ መመሳሪያ መሳሪያዎችም ሆኑ ሌሎች ተመሳሳይ መገልገያዎች ተበላሽተው አገልግሎቱ እንዳይቋረጥ መጠባበቂያ መሳሪዎችን እንዲኖሩት ያደርጋል ቢበላሹም በራሱ ወጭ ያስጠግናል።
7. የመጠጥ ውሃ አገልግሎት ማሻሻያ ወይም ማስፋፊያ ስራ መስራት ሲያስፈልገው ቢሮው በሚያዘጋጀው ስታንዳርድ ዲዛይን መሠረት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል ውሳኔ ሲያገኝ ተግባራዊ ያደርጋል።
8. በስሙ ይከሳል ይከሰሳል ውል ይዋዋላል የንብረት ባለቤት ይሆናል።
9. አላማውን ከግብ ለማድረስ ሌሎች ህጋዊ ተግባራትን ያከናውናል።

አንቀጽ 12

ስለ ጽ/ቤቱ ኃላፊ ስልጣንና ተግባር

የጽ/ቤቱ ኃላፊ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. ጽ/ቤቱን በኃላፊነት ይመራል ይቆጣጠራል
2. በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል ያስተዳድራል ያሰናብታል።
3. የጽ/ቤቱን አመታዊ የስራ እቅድና በጀት በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል ሲፈቀድ በስራ ላይ ያውላል።
4. በጽ/ቤቱ ስም የባንክ ሂሳብ ይከፍታል ያንቀሳቅሳል።
5. ጽ/ቤቱን በሶስተኛው ወገን ዘንድ ይወክላል፡
6. መደበኛ የስራ ሪፖርትቶችን በየ 3 ወሩ ለቦርዱ ያቀርባል፣
7. በቦርድ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

በንዑስ ከተሞችና ገጠር ቀበሌዎች የንፁህ መጠጥ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ስለማደራጀት

አንቀጽ 13

አደረጃጀትና ተጠሪነት

1. የንዑስ ከተሞችና ገጠር ቀበሌዎች የውሃ አገልግሎቶች

   ሀ/ በወረዳው መስተዳድር ም/ቤትና በተጠቃሚው ሕዝብ በጋራ የሚቋቋም ሰባት አባላት ያሉት የውሃ ኮሚቴ

   ለ/ የጣቢያ ሠራተኞች ይኖራቸዋል።

2. የንዑስ ከተሞችና ገጠር ቀበሌዎች የውሃ አገልግሎቶች ኮሚቴ ተጠሪነት ለቀበሌ መስተዳድር ም/ቤት ሲሆን በቴክኒክ ጉዳዮች ላይ ተጠሪነታቸው ለወረዳ የውሃ ሃብት ጽ/ቤት ይሆናል።
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የውሃ አገልግሎት ኮሚቴው ሰብሞር ተገልጋዮ ሕዝብ የሚመርጣቸው የውሃ ተጠቃሚዎች መሆን አለባቸው።
4. የኮሚቶው አባላት የስራ ዘመን ሁለት አመት ይሆናል። በየሁለት አመትም የኮሚቴ አባላት የመምረጥ ስራ ይካሄዳል።

አንቀጽ 14

የውሃ ኮሚቴው ስልጣንና ተግባር

ኮሚቴው ከዚህ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል

1. የመጠጥ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጣቢያን የእለት ከእለት ስራ የሚያከናውኑ ሠራተኞችን በስምምነት ይቀጥራል ያስተዳድራል ይቆጣጠራል ያሰናብታል።
2. ኮሚቶው የውሃ ጣቢያዎችን በበላይነት ያስተዳድራል ከአቅም በላይ የሆኑ ጉዳዮች ሲኖሩ ለወረዳው የውሃ ሃብት ጽ/ቤት እያቀረበ ያስወስናል።
3. ከወረዳው መስተዳድር ም/ቤት ጋር በመነጋገር ለጣቢያ ሠራተኞች ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል።
4. የውሃ ጣቢያዎችን ተገልጋዮ ህብረተሰብ በራሱ ተሳትፎ እንዲጠብቃቸውና እንዲንከባከባቸው ያደርጋል።
5. መደበኛ የመሳሪያዎች ጥገናና ጥበቃ ይፈጽማል፣

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 15

በሌላ ይዞታ መስመር የመዘርጋትና የማስተላለፍ መብት

1. በፍትሐ ብሔር ህግ ቁጥር 1220 እንደተደነገገው ባለቤቱ ወይም በሊዝ ያዥው በመጠየቅና ተገቢውን ካሳ በቅድሚያ በመክፈል ከባለቤቱ ወይም ከሊዝ ያዥ ጋር በሚደረገው ስምምነት መሠረት ጽ/ቤቱ የውሃ መስመሮችን ለመዘርጋትና ለማስተላለፍ በግል ንብረት ወይም ይዞታ ለመጠቀም ይችላል ሆኖም ባለንብረት ወይም ባለ ይዞታው ወይም ቢል ያዥ ያለ ጽ/ቤቱ ፈቀድ የተዘረጉ መስመሮችን ለማንሳት አይችልም።
2. ለተዘረጉ የውሃ መስመሮች በሊዝ በያዘው ወይም በሚጠቀምበት ባለንብረት ላይ ማለፋን እንዲያውቅ የተደረገ የቢል ያዥ ወይም ሌላ ሕጋዊ ተጠቃሚም እንደንብረት ባለቤት ሆኖ የተዘረጉ መስመሮችን የመጠበቅ ኃላፊት አለበት።
3. ማንኛውም ባለንብረት፣ ባለይዞታ ወይም ቢል ያዥ ጽ/ቤቱ መስመሮቹን ለመዘርጋት ለመጠቀም ለመቆጣጠር ለመንከባከብ ወይም ለመጠገን የሚያደርገውን ስራ ማደናቀፍ የለበትም።

አንቀጽ 16

ጐዳናዎችና መንገዶች ላይ መስመሮችን የመዘርጋት መብት

ጽ/ቤቱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች በማሟላት በአውራ ጐዳናዎችና መንገዶች ላይ የውሃ መስመሮችን የመዘርጋት የማደስ ወይም የመትከልና በዚሁ ስራ እንደ አስፈላጊነቱ መንገዶቹን የመቆረጥ ወይም የመቆፈር መብት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል። ሆኖም፦-

ሀ/ አስቸኳይ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር ስራውን ከመጀመሩ ከሶስት ወራት በፊት በጽሁፍ ማስታወቂያ በመስጠት ከሚመለከታቸው የመንግስት አካል ወይም የመንገድ ባቤት ፈቃድ ማግኘት አለበት ይሆንና በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካል ወይም የመንገድ ባለቤት ፈቃድ ባይሰጠውም መስራት ይችላል።

ለ/ መንገዶቹና ጐዳናዎቹን ለመጠገን የሚደረገው ማንኛውንም ወጭ ጽ/ቤቱ የመሸፈን ግዴታ አለበት።

አንቀጽ 17

የከተማውን መሪ ኘላን ስለመከተል

ጽ/ቤቱ በከተማው ውስጥ የውሃ ስራዎቹን የሚገነባው ወይንም የሚዘረጋው የከተማውን መሪ ኘላን በመከተል ይሆናል።

አንቀጽ 18

የውሃ አገልግሎት ጽ/ቤት ከተለያዩ መስሪያ ቤቶች ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት

ጽ/ቤቱ በተቋቋመበት የከተማ ክልል ውስጥ ከሚገኙ የመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ጤናማ የሆነ የስራ ግንኙነት ይኖረዋል። ስራዎችን በመግባባትና በመተጋገዝ እንዲሰሩም ይጥራል።

አንቀጽ **19**

የበጀት ምንጭ

1 ኛ/ የውሃ አገልግሎት ጽ/ቤቶችም ሆኑ የውሃ ጣቢያዎች /ኮሚቴ/ የበጀት ምንጫቸው

ሀ/ ከውሃ አገልግሎት ክፍያ

ለ/ ከውሃ ሽያጭ የሚሰበሰብ ገቢ

ሐ/ ከአገልግሎት ልዩ ልዩ ንብረት ሽያጭ የሚገኝ ገቢ

መ/ ከመንግስትና ከድርጅቶች ከሚገኝ ስጦታና እርዳታ

ሠ/ ከተጠቃሚ ህብረተሰብ መዋጮ

አንቀጽ **20**

ስለ ገቢ አጠቃቀምና የገንዘብ አስተዳደር ስርዓት

እያንዳንዱ የከተማ የውሃ አገልግሎት ጽ/ቤትና የገጠር ውሃ ኮሚቴ

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18 መሠረት የሚሰበሰበውን ገቢ ለታቀደለት አላማ የማዋል ግዴታ አለባቸው።
2. የገንዘብና የንብረት አስተዳደራቸው በክልሉ መንግስት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የሚፈፀም መሆን አለበት።
3. ትክክለኛና የተሟላ የሂሳብ መዛግብት ይይዛሉ።
4. የሂሳብና ገንዘብ ነክ ሰነዶቻቸው በየጊዜው በክልሉ ዋና ኦዲተር መ/ቤት ወይም እሱ በሚወክለው አካል ይመረመራሉ።
5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የንዑስ ከተማና ገጠር ቀበሌ የውሃ ኮሚቴን የሂሳብ አያያዝ በተመለከተ የወረዳው መስተዳድር ም/ቤት በሚመርጠው አካል ሊያስመረምር ይችላል።
6. የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞቻቸውን በተመለከተ ቢሮው በሕግ እውቅና ባለው ማተሚያ ቤት አሳትሞ ለቁጥጥርና ክትትል አመች በሆነ ሁኔታ ያሰራጫል ሕትመቶቹም

ሀ/ የሕዝብ ውሃ ሽያጭ ቦኖዎች የመሸጫ ትኬቶች

ለ/ የደንበኞች የአገልግሎት ክፍያ መሰብሰቢያዎችና ሌሎች የውሃ አገልግሎት ክፍያ መቀበያ ደረሰኞችን ያካትታል።

አንቀጽ 21

ስለ ሠመራ ሎጊያ የውሃ አገልግሎት

1. የሠመራ ሎጊያ የውሃ አገልግሎት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 መሠረት ተግባራዊ እስከሚሆን ቢሮው ከተለያዩ አካላት ጊዜያዊ ቦርድ ሊያቋቁም ይችላል።
2. ጊዜያዊ ቦርድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ስር የተዘረሩ ስልጣንና ተግባራት እንዲሁም ለዋናው ቦርድ የተቀመጡትን ሌሎች አንቀጾች እንደ አግባቡ ይጠቀምባቸዋል።
3. የጊዜያዊ ቦርድ ተጠሪነት ለቢሮው ይሆናል።

አንቀጽ 22

መብትና ግዴታዎች ስለማስተላለፍ

ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የከተማና ገጠር ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤቶች ያፈራቸው ንብረቶች ያገኛቸው የባለቤትነት መብቶች የገቧቸው እዳዎችና ሌሎች ግዴታዎች በሙሉ በዚህ አዋጅ ለተቋቋሙትና እንደገና ለተደራጁት የከተማና የገጠር ውሃና ፍሳሽ አገልግሎቶች ተላልፈዋል።

አንቀጽ 23

ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

1. ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዱ ደንቦች የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ሊያወጣ ይችላል።
2. ይህን አዋጅና ወደፊት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚረዱ ዝርዝር መመሪያዎችን ቢሮው ሊያወጣ ይችላል።

አንቀጽ 24

ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጐች

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ህግና ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

አንቀጽ 25

አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከፀደቀበት ከየካቲት 22/2000 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሠመራየካቲት 22 /2000 ዓ.ም

እስማኤል አሊ ሲሮ

የአፋር ብ/ክ/መ/ርዕሰ መስተዳድር

a

Ismaqil Qali sirro

Samara

Ismaqil Qali sirro

Qa/Ag